# የACPS Express 9/23/2022: የሴፕቴምበር (September) - የ‘ACPS’ ተማሪ እና ሠራተኛን እውቅና-መስጠት

## የሴፕቴምበር (September) - የ‘ACPS’ ተማሪ እና ሠራተኛን እውቅና-መስጠት




### ‘EVERFI Empowered Seal’ ተቀባይ

በኖርዝ አሜሪካ - በዚህ ዓመት ለ10% በዲስትሪክቶች ዙሪያ ለሚገኝ ትምህርት ቤት የተሰጠው-ሽልማት - የEVERFI's 2022 Empowered District Sealን፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) አግኝቷል። ይህ ስየማ ሊገኝ የሚችለው፤ ታይቶ-የማይታወቅ ቁርጠኝነትን ለሁሉም የልጅ ትምህርት - በEVERFI ፕሮግራሞች ጥቅም-ውስጥ የሚታዩ-በሆኑት - በK-12 የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ውስጥ እና በየግል-ትምህርት ቤቶች ውስጥ ብቻ የሚገኝ-ይሆናል።

የ‘EVERFI’ ፕሮግራሞች፤ ተማሪዎችን በበርካታ ጉዳዮች ላይ - የገንዘብ-አያያዝ ትምህርት፣ ማህበራዊ-ስሜታዊነት (Social-Emotional) ትምህርት እና የኮሌጅ እና የስራ-መስክ ዝግጁነትን ጨምሮ - መረጃ-ለመስጠት እና ኃይል-እንዲኖራቸው የሚረዳ-ነው። ይህ ሙሉ የሆነ የልጅ አቀራረብ፤ በK-12 ዓመቶቻቸው ወቅት እና ከዚያም-ባለፈ ሁኔታ፣ ተማሪዎች ስኬታማ በሆነ መንገድ እና ጤናማ በሆነ መንገድ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ የሚያደርጋቸው ነው። ይህ፣ እንደ ‘ACPS’ የስራ-መስክ እና የቴክኒካዊ ትምህርት (Career and Technical Education (CTE) ውስጥ አንዱ-አካል ሆኖ ጥቅም-ላይ ይውላል።

"የCTE አስተማሪዎች - በእውነተኛው ሕይወት የችሎታ ስልጠናን - አሁን ባለው የ‘CTE’ የፕሮግራም አካባቢ ካሪኩለር ላይ የሚጨምረው እና በገንዘብ እና በሕይወት ውሳኔዎች ላይ የሚያደርጉት ማወቅን በመጨመር፣ ከ‘EVERFI digital resources’ ጋር አጣምረው በትጋት ሲሰሩ-ነበር፤ " ብለዋል የACPS - የ‘CTE and Workforce Development’ ዳይሬክተር፣ ዶ/ር ትሪሲአ ጄኮብስ (Dr. Tricia Jacobs)።

የ‘EVERFI’ ፕሮግራምን እና የመግቢያ ቅጹን ያጠናቀቁ ከ‘Empowered Seal districts’ የመጡ ተማሪዎች፤ በዚህ ዓመት - እስከ $1,000  የሚደርስ ስኮላርሽፖችን ለመሸለም ብቁ-ናቸው።

# አምስት የካፊቴሪያ ሠራተኞች - የትምህርት ቤት ምሣ ጀግኖች ተብለው ተሰይመዋል



በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፣ በየቀኑ ምግቦችን በካፊቴሪያ ውስጥ በማቅረብ፤ አምስት የትምህርት ቤት አገልግሎቶች (School Nutrition Services) አባላቶች - አሁን በ'No Kid Hungry School Lunch' ጀግናዎች የ'Virginia Hall of Fame' በመሆን ክብርን-አግኝተዋል።

እነዚህ የACPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ከኮፊያዎች (capes) ይልቅ - ሽርጦችን (aprons) የሚለብሱ ሲሆን፣ ነገር ግን ረሃብን ለመዋጋት በትምህርት ቤት ካፊቴሪያዎች ውስጥ በሚሰሩት-ስራ ግን የጀግና-ጀግና (superhero) ናቸው:

- ሻይዳ ሙስታፋ (Shadia Mustafa)፣ የካፊቴሪያ አስተናጋጅ፣ በዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሚርታ ናቫሬት (Mirtha Navarrete)፣ የካፊቴሪያ (Cafeteria) ማናጀር፣ በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት
- ሎራ ፑርዲ (Laura Purdy)፣ የካፊቴሪያ (Cafeteria) ማናጀር፣ በላየልስ-ክራውች ትራድሽናል አካዳሚ (Lyles-Crouch Traditional Academy)
- ማርታ ዊስኒውስክ (Marta Wisniewska)፣ የካፊቴሪያ (Cafeteria) ማናጀር፣ ማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት
- ሚርና ዛለስ (Mirna Zalles)፣ የካፊቴሪያ (Cafeteria) ማናጀር፣ ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት

እነዚህ-ሁሉም የካፊቴሪያ ሠራተኛ አባላቶች፤ የተወሰነ ለእያንዳንዱ ልጅ ጤናማ እና ተመጣጣኝ ምግቦችን በየቀኑ እንዲያገኙ የሚችሉትን-ሁሉ የሚያደርጉ-ናቸው።

የአንድ የካፊቴሪያ ማናጀር የሆኑት ታሪክ በማገናኘት፤ የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት፣ ርዕሰ-መምህር ዶ/ር ኢንግሪድ ባይነም (Dr. Ingrid Bynum) ሲገልጹ - ዛለስ (Zalles) እንዴት ለአስተዳደሩ ስለ "ልባቸውን ስለነካው ልዩ የሆነ ልጅ/special child who touched her heart" ለመናገር እንደመጡ ገልጸዋል። ዛለስ (Zalles)፣ በምሣ ሰልፍ-ላይ ለሁለተኛ ምሣ የሚመጡ የተማሪ ቤተሰቦች በቂ-ምግብ በመኖሪያ-ቤታቸው ውስጥ መኖሩን የሚረጋገጥበትን መንገድ ትምህርት ቤቱ እንዲረዳ-በመጠየቅ፣ ከሚቻለው-ሁሉ በላይ በመሄድ ጥያቄያቸውን አቅርበዋል። እነዚህ ነገሮች ናቸው - የACPS የአመጋገብ አገልግሎቶች ቡድን አባላቶች - ስራቸው-በትክክል እንዲቀጥል እና የትምህርት ቤት የምሣ ጀግናዎች ሊያደርጋቸው የቻለው።

# በACHS ውስጥ፣ የ‘National Merit Scholarship’ ለፍፃሜ የደረሱ (Semifinalist)



በ2023 የ‘National Merit® Scholarship Program’፣ በግምት 16,000 ከሚሆኑ የግማሽ-ፍፃሜ አሸናፊ-ሆነው ከደረሱ ተወዳዳሪዎች መካከል፤ ለናታኔኤል ፒ. በርክሄድ (Nathaniel P. Burkhead) - የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ሲኒየር (senior)ን እንኳን-ደስ አለህ-እንላለን። ናታኔኤል (Nathaniel)፣ በፊዚክስ እና በሂሳብ ግንኙነት ባለው የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ (post-secondary) ለመቀጠል ዕቅድ አለው። የ‘avid learner’ ሲሆን፣ ለዶክትሬት ዲግሪ ለመቀጠል - ምኞት አለው። “ቤተሰቦቹ እንዲኮሩበት ለማድረግ እና ያደረገውን መስዋዕትነቶች በመቀጠል ላይ እያለ - የቀለም-ትምህርት ስኬቶቹን በማጉላት ይህን እውቅና በማግኘቱ - ናታኔኤል (Nathaniel) ደስተኛ-ነው”፣ ብለዋል የACHS የትምህርት ቤት ማማከሪያ (School Counseling) ዳይሬክተር - አር. ብሪአና ሃርዳዌ (R. Briana Hardaway)።

ከአገር-አቀፍ የሚውጣጡት የግማሽ-ፍፃሜ አሸናፊዎች (semifinalists) - በ68ኛው ዓመታዊ የ‘National Merit Scholarship Program’ ውስጥ - ከአሜሪካ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲኒየሮች (U.S. high school seniors) ውስጥ፣ ከአንድ-መቶኛው ያነሰውን የሚወክል ነው። የግማሽ-ፍፃሜ አሸናፊዎች (semifinalists) - ከሚገባው-በላይ ግሩም የሆነ የቀለም-ትምህርት ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጊዜያቸው ውስጥ ያላቸው መሆን፣ በከፍተኛ ትምህርት ቤት ሹሞች ስማቸው የተመረጠ እና ድጋፍ-ያገኙ መሆን፣ ጽሁፍ (essay)፣ እና የተማሪው የቀደመ ክንውኑን የሚያረጋግጠውን - የ‘SAT® ወይም የACT® ውጤቶችን ያገኘ መሆን አለበት።

እነዚህ በቀለም-ትምህርታቸው ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎች፤ አሁን - በግምት የ7,250 የNational Merit Scholarships የሚያስገኘውን ወደ $28 ሚሊዮን የሚጠጋውን - ሽልማት በሚቀጥለው ፀደይ-ወቅት (spring) እንዲያገኙ-ለማስገባትና ለማጠናቀቅ ዕድል አላቸው። ወደ 95 በመቶ የሚሆኑ የግማሽ-ፍፃሜ ተወዳዳሪዎች (semifinalists)፤ ወደ መጨረሻው ደረጃ እንደሚካፈሉ የሚጠበቅ እና በግምት-ግማሽ የሚሆኑ በመጨረሻ-ደረጃ ላይ የደረሱ፤ የ‘National Merit Scholarship’ን አሸንፈው፣ የ‘Merit Scholar title’ን ያገኛሉ። የመጨረሻ-አሸናፊዎች፤ በፌብሩዋሪ (February) ወር ውስጥ የምናሳውቅ-ይሆናል። ለ2023 - የ‘National Merit Scholarship’ አሸናፊዎች፤ በአራት አገር-አቀፍ ጋዜጣዊ-መግለጫዎችን - በኤፕሪል (April) ወር መጀመሪያ ላይ ጀምሮ፣ እና በጁላይ (July) ወር ውስጥ ይጠናቀቃል።

# ከወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - የሚቻለውን-ሁሉ ማግኘት




የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፤ በተማሪው የትምህርት ቤት ሕይወት እና በመኖሪያ-ቤት ሕይወቱ መካከል ያለውን አስፈላጊ-የሆኑ ግንኙነቶችን የሚፈጥር-ነው። ACPS፤ የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶችን፣ በየ-የትምህርት ዓመቱ የቀን-መቁጠሪያ ሁለት ጊዜ በማካሄድ፣ ቤተሰቦች እና አስተማሪች ስለተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የእድገት-ሂደት ላይ ለመወያየት ዕድሎችን ይሰጣቸዋል።

ለ2022-23 የትምህርት ዓመት፣ የበልግ (fall) የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለሁለተኛ-ደረጃ (መካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ቤተሰቦች - በሴፕቴምበር (Sept.) 29 ቀን 2022 እና በሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ላይ ይካሄዳል። ለሣሙዔል ተከር (Samuel Tucker) ቤተሰቦች፤ ኮንፈረንሶች - በኦክቶበር (Oct.) 13 ቀን 2022፣ እና በኦክቶበር (Oct.) 14 ቀን 2022 ላይ ይካሄዳል። ሌሎች ሁሉም የመጀመሪያ-ደረጃ ኮንፈረንሶች - በኖቬምበር (Nov.) 3 ቀን 2022፣ እና በኖቬምበር (Nov.) 4 ቀን 2022 ላይ የሚካሄዱ-ይሆናል። ስለ ኮንፈረንሶቹ የጊዜ ሰሌዳ እና ተያያዥ-የሆኑ ሎጂስቲኮችን በተመለከተ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

ከወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ የበለጠ-ተጠቃሚ ለመሆን፤ የACPS፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ ማዕከል (Family and Community Engagement Center (FACE)፤ የሚከተሉትን በምክር-መልክ ያቀርባል:

- **ተዘጋጁ (Get Ready)**: አብዛኛዎቹ የACPS ትምህርት ቤቶች፤ የ'ParentSquare' የጊዜ-ሰሌዳ የኮንፈረንስ ጊዜያቶችን ለቤተሰቦች ይጠቀማል። ቀልጣፋ እና ቀላል የምዝገባ ሂደት መኖሩን ለማረጋገጥ፤ በ'ParentSquare' አካውንታችሁ መመዝገባችሁን አረጋግጡ እና አፕ (app) ዳውንሎድ ማድረግዎን እርግጠኛ ሁኑ።
- **ሁሉንም ሰው በአንድ-ገጽ ላይ ማምጣት**: ልጅዎ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ እና የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪ ካለው/ላት፤ ሁለቱም በኮንፈረሱ ውስጥ እንዲገኙና የተማሪዎ የእርዳታ ቡድን ግንኙነት እንዲያደርጉ መጠየቅ-ትችላላችሁ።
- **ጥያቄዎችን ጠይቁ**: የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - በአጠቃላይ ከ10-15 ደቂቃዎችን ይወስዳል። ከስብሰባው አስቀድማችሁ፣ ለአስተማሪው ማቅረብ የምትፈልጓቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር አውጡ። አስፈላጊ-ከሆነ፣ በማንኛውም ጊዜ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ ለመጠየቅ አትፍሩ።
- **ማስታወሻዎችን ውሰዱ**: በኮንፈረንሱ ጊዜ፤ ቀናቶችን ፃፉ፣ የተጋሩ-ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና የአስተማሪው ለጥያቄዎ-ሰጡትን መልስ ፃፉት።
- **ልጅዎን ያሳትፉ — ከስብሰባው - በፊት እና በኋላ**: አስቀድመው - ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩበት፤ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የሚወዱት የትምህርት-ዓይነት እና እንቅስቃሴ ምን እንደሆነ ጠይቁ፤ እንዲሁም፣ የማይወዱትስ ምንድነው፣ ለምን - ብላችሁ ጠይቁ። ከዚያ-በኋላም፤ ምን እንደተማራችሁ እና ከትምህርት ቤት ጋር ልጅዎን ወደ ስኬት እንዲደርስ ለመርዳት ምን-እንደምታቅዱ አጋሩ።

ብዙ የACPS ቤተሰቦች፤ በ'ParentSquare' ድህረ-ገጽ፣ በኢሜል ማገናኛ (email link፣ በቴክስት ማገናኛ (text link) ወይም በአፕ (app) ማስታወቂያዎች - አማካኝነት ወደ ኮንፈረንሶቹ ለመመዝገብ (sign up) ለማድረግ የሚችሉ-ይሆናል። እባክዎን፤ እነዚህን ደረጃ-በደረጃ የሚወሰዱ መመሪያዎችን አመላክቱ:
in English (PDF) | en español (PDF) | አማርኛ (PDF) | بالعربية (PDF)

በ'ParentSquare' ውስጥ - ለሠራተኞች፣ የጊዜ-ሰሌዳን መያዝ-ምን እንደሚመስል ለመመከት ያህል፤ ይህን የstep by step guide ማጎልበቻን በ'ACHS Technology Integration Support team' የተዘጋጀውን፤ እባካችሁ ተመልከቱ።

## የACPS የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) እና የፍትሃዊ-እኩልነት፤ ዴኒ ስካት (Deneé Scott)ን - እንደ ከK-12ኛ ትምህርት ቤት ካውንስሊንግ አድርጎ፤ እንኳን-ደህና መጡ ብሉ ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ዴኒ ስካት (Deneé Scott)ን - ለክፍሉ/division - እንደ ከK-12 የትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያሳውቅ-ደስታ ተሰምቶታል። ከዚህ-ቀደም፤ በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ውስጥ፣ ስካት (Scott) - እንደ የካውንስሊንግ ዳይሬክተር (Director of Counseling) ሆነው ያገለገሉ እና፤ በስራ-መስካቸው ጊዜ ውስጥ-ሁሉ ለፍትሃዊ ዕኩል የሆኑ ዕድሎች እና ውጤቶችን ለመፍጠት ቅድሚያ-የሰጡ ናቸው።

በሃመንድ (Hammond) ውስጥ፣ ስካት (Scott) - የትምህርት ቤት ካውንስለር-የሚያደርጉ ቡድንን - እውቅና-ያለው የASCA ሞዴል ፕሮግራም እንዲሆን - በአሜሪካ የትምህርት ቤት ካውንስለር ማኅበር በኩል የመሩ ናቸው። የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (SEAL) ስርዓተ ትምህርት ለማስፈጸም፣ እና ሁሉንም ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ባለብዙ-ደረጃዎች የስርዓተ እገዛ (Multi-Tiered System of Support (MTSS) ሂደት አማካኝነት ፍላጎቶቻቸውን የማገዝ ጥረትን በመምራት፤ ለሃመንድ (Hammond) - ዓይነተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው። ስካት (Scott)፣ በመጀመሪያ-ደረጃ እና በኮሌጅ ደረጃዎች ያስተማሩ ሲሆን፤ የመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካውንስለር የነበሩ፣ እና እንደ የመካከለኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የካውንስለር መሪ ሆነው አገልግለዋል።

ስካት (Scott)፣ የባችለውር እና የማስተርስ ዲግሪያቸውን በትምህርት - ከኦስዌጎ ስቴት ዩኒቨርስቲ (Oswego State University) እና የማስተርስ-ዲግሪያቸውን በካውስሊንግ እና በሰው-ልጅ እድገት - ከጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። በአሁኑ-ጊዜ፤ በማህበረሰብ እንክብካቤ እና በካውንስሊንግ - በሊበርቲ ዩኒቨርስቲ አማካኝነት የዶክትሬት ዲግሪያቸው እያጠናቀቁ-ይገኛሉ።

# የACPS የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) መምሪያ እና ፍትሃዊ-እኩልነት (Equity)፤ እንደ የተማሪ እርዳታ ቡድን ዋና ዳይሬክተር አድርጎ - ዶ/ር ቪክተር ማርቲን (Dr. Victor Martin)ን ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ዶ/ር ቪክተር ማርቲን (Dr. Victor Martin)ን እንደ የትምህርት ቤት - የተማሪ እርዳታ ቡድን - አዲስ ዋና ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያስታወቅ-ደስታ ይሰማዋል። ወደዚህ የስራ-ድርሻው፣ ከሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 ጀምሮ - አሁን ካለበት የስራ-ድርሻ ከሆነው - በአሌክሳንድርያ ውስጥ፣ የኖርዘን ቨርጅኒያ የታዳጊዎች ማቆያ (Juvenile Detention) ማዕከል - ርዕሰ-መምህርነት የሚሸጋገር ይሆናል። ከዚህ-ቀደም፤ ዶ/ር ማርቲን (Dr. Martin)፣ እንደ የመጀመሪያ የACPS የፍትሃዊ-እኩልነት ዳይሬክተር፣ እንዲሁም የአማራጭ ፕሮግራሞች እና ፍትሃዊ-እኩልነት ዳይሬክተርም ነበሩ። የ'ቻንስ ፎር ቼንጅ አካዳሚ (Chance for Change Academy)'፣ ርዕሰ-መምህርም ነበሩ። በተጨማሪም፤ በጆርጅታውን ዩኒቨርስቲ ውስጥ በየታዳጊዎች የፍትህ እና ተሐድሶ ማዕከሉ (Center for Juvenile Justice and Reform) በሆነው ውስጥም ሰርተዋል።

ዶ/ር ማርቲን (Dr. Martin)፣ ዓለም-አቀፍ የማስተማር ልምድ፣ ለእንግሊዘኛ ማግኛ ፕሮግራም በቻይና ውስጥ ዋና-መሪ አስተማሪ ሆነው ያገለገሉ፣ እና ከአሜሪካ የትምህርት መምሪያ ጋር ከትምህርት ስርዓት ጋር በ'Pine Ridge Reservation' ውስጥ በ'ሳውዝ ዳኮታ (South Dakota)' ውስጥ ሰርተዋል። እንደ አስተማሪ በመሆን - ዶ/ር ማርቲን (Dr. Martin)፣ በፕሪንስ ዊሊያም ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቨርጅኒያ እና በሳን ዲያጎ፣ ካሊፎርኒያ ውስጥ - የማስተማር የስራ-መስካቸውን በጀመሩበት ቦታ ሰርተዋል።

ዶ/ር ማርቲን (Dr. Martin)፣ ከኦስዌጎ ስቴት ዩኒቨርስቲ (Oswego State University) በኒው-ዮርክ (NY) ውስጥ እንግሊዘኛን ሜጀር-አድርገው ባችለር-ዲግሪያቸውን ያገኙ እና፣ ከጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ - በትምህርት አመራርነት የማስተርስ-ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በ2013 ውስጥ፣ በብሄራዊ ተቋም - ለከተማ ትምህርት ቤት አመራሮች - በሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ - ማህበርተኛ ነበሩ። በትምህርት አመራርነት (educational leadership)፣ ከፔንሲልቬኒያ ዩኒቨርስቲ - ዶክትሬታቸውን አግኝተዋል።

ዶ/ር ማርቲን (Dr. Martin)፣ በቨርጅኒያ አማራጭ የትምህርት ማኅበር (Virginia Alternative Educators Association) ቢሮ ያላቸው እና ለMSAN - በ'Research Council) አባል-ናቸው። በተጨማሪም - ተባባሪ-ደራሲ የነበሩም ሲሆን፤ በ'Strategies in Action: A Collection of Classroom Applications, Volume 1 (2009). አዲስ ርዕሰ-መምህር፣ ለሰሜናዊ ቨርጅኒያ የታዳጊዎች ማቆያ (Juvenile Detention) ማዕከል፣ በመጪው ወራቶች ውስጥ የሚመረጥ-ይሆናል።

# ‘SEAL’ በስራ-ላይ ሲውል: ኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት፤ ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂ




በትምህርት ዓመቱ-ወቅት ሙሉ፤ ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች፤ ተጨማሪ የትምህርት-አሰጣጥ - በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) ያገኛሉ። በየቀኑ-የሚሰጠው የ30 ደቂቃዎች የSEAL ጊዜ፤ ተማሪዎችን - በግንኙነት-በመፍጠር ችሎታዎች፣ ኃላፊነት ያለው ውሳኔ በመወሰን፣ እራስን-በማወቅ፣ እራስን በመቆጣጠር እና በማህበራዊ ግንዛቤዎች የሚረዳቸው ነው። የስርዓተ ትምህርቱ ቁሳቁሶች የተቀረጹት - በክፍል/division፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚያደርገው ማስተከከያ መሠረት - ልዩ ፍላጎቶችን የሚፈልጉትን በትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው ውስጥ ለመርዳት የተቀረጸ ነው።

የACPS - የግንኙነቶች ቢሮ በቅርብ-ጊዜ - የኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት፤ ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂን፤ ተማሪዎች ኃላፊነት የተሞላው ውሳኔዎች እንዲያደርጉ እና ስሜቶቻቸውን እንዲገልጹ ጉልበት-ለመስጠት - እንዴት SEAL እንደረዳቸው ተስተውሏል።




ዛሬ፤ ምን ይሰማሃል/ሻል? ያልተመቻቸ-ስሜት፣ ወይም የተመቻቸ ስሜት? ከፍተኛ-ጉልበት ያለው ስሜት ወይም ዝቅተኛ-ጉልበት ያለው ስሜት? የሚሰማችሁን ስሜት ፈልጎ-አውቆ እና በስሜት-ሁኔታን መለኪያው (mood meter) ላይ የት-እንደሚገኝ ማወቅ፣ ወደ ቀናችሁ በቀላሉ የመግቢያ ጥሩ-መንገድ ነው። በቀደመው-ሰዓት - በሰኞ ጠዋት ላይ፣ ብዙ ናንሲ ባከር (Nancy Baker) ክፍል ውስጥ የሚገኙ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ድካም-የተሰማቸው ነበሩ፤ ነገር ግን ጥቂቶቹ የሚያስደስት ፊት፣ በጥሩ-ሁኔታ ያሉ፣ ደስተኛ፣ የተረጋጋ እና ሰላማዊ-የሆነ ስሜት ነበራቸው።

ቁርስ-ከበሉ በኋላ፣ ተማሪዎች በክፍላቸው ፊት-ለፊት ላይ ወደስራቸው የሚያስጀምራቸውን፣ ክብ-ሰርተው ነበር።  የSEAL ችሎታዎቻቸውን በስራ-ላይ የሚያውሉበት ጊዜ ስለነበረ - መጪውን የትምህርት ቤት የመስክ ጉዞ (field trip) እና ከተማሪ ባህሪያቶች በመስክ ጉዞው (field trip) ወቅት የሚጠበቅባቸውን - ተወያይተው ነበር።



ባከር (Baker) በኮራ ኬሊ ኩገርስ (Cora Kelly Cougars) ስላለው ክፍላቸው - እንዴት ‘ROAR’ የሚለው ምዕፃረ-ቃል ለ—Respectful, Our Best, Always Safe, Responsible — የሚለው - በአውቶቡስ ውስጥ እንዴት የሚጠበቅባቸውን ባህሪይ እንደሚያስቀምት ገልጸዋል። በማስከተልም - የሞ ዊለምስ (Mo Willems) መጽሐፍ “Don’t Let the Pigeon Drive the Bus”  - (It’s safe to say the pigeon might need a SEAL refresher course.) ቪዲዮውን አስከትለዋል። ተማሪዎች እንዴት ለራሳቸው ጥሩ ምርጫዎችን ማድረግ እና ሌሎች በዙሪያቸው የሚገኙትን እንዴት ማክበር እንዳለባቸው  - እንደ አክባሪ መሆን እና ሁልጊዜ “አመሰግናለሁ/thank you” ማለትን ማስታወስ-እንዳለባቸው - መጽሐፉ እንዴት እንደሚረዳ፣ በማጤን ባከር (Baker) ገልጸዋል።



ከዚያ ጊዜው ተማሪዎች ተነስተው ወደ ጠረጴዛቸው ሄደው በSEAL ጆርናላቸው ላይ የሚጽፉበት፣ በመስክ ጉዞ (field trip) ላይ እያሉ ‘ROAR’ን እንዴት በልምድ-ላይ ማዋል የሚችሉበትን ሁለት መንገዶችን ይገልፃሉ። ተማሪዎች፤ ምሳሌዎችን እንደ - “በደህንነት ቆይ/stay safe”፣ “በመቀመጫህ-ላይ ቆይ/stay in my seat”፣ “በዝግታ-ተናገር/speak calmly” እና “በአውቶቡስ ውስጥ ድብድብ-የለም/no fighting on the bus” የሚረዱበት-ይሆናል።

የተማሪዎች -  በባከር (Baker) ክፍል ውስጥ፤ SEAL - ስሜቶቻቸውን ለማጋራት፣ ሃሳባቸውን ለመግለጽ፣ የተረጋጋ-ለመሆን እና በራቸው ላይ ትኩረት ለማድረግ የረዳቸው መሆኑን - ሁሉም በአንድላይ ተስማምተዋል። ባከር (Baker) በዚህ በመስማማት ሲያክሉበት፤ “የሚሰማቸውን ስሜት መለኪያዎች (mood meters)… የሚወዱት ይመስለኛል፤ ስለዚህ ምን እንደሚሰማቸው ማጋራታቸው የሚያስፈልግ እንደሆነ ተመልክቼአለሁ።”

# ዝቅተኛ-ክፍያ ያለው ኢንተርኔት መገኘት - ለነፃ ወይም ቅናሽ-ዋጋ ያለው፣ ብቁ-ለሆኑ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች




አዲስ ፕሮግራም የሆነው፤ የAffordable Connectivity Program (ACP)፤ በአነስተኛ የኢንተርኔት የክፍያ-ዋጋ - ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች - ለነፃ ወይም ቅናሽ-የተደረገላቸው ምግቦችን ለማግኘት ባለፈው 12 ወራቶች ውስጥ ብቁ ለሆኑ መገኘት-የሚችል ነው።

'ACP'፣ ብቁ-ለሆኑ ቤተሰቦች - ለኢንተርኔት ቅናሽ-ክፍያ የሚያደርግላቸው ይሆናል። ብቁነት-ሊገኝ የሚችለው ከሚከተሉት ሁለት-መንገዶች በአንደኛው ነው:

- በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኘው ልጅ፤ ለነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) - በትምህርት ቤት የቁርስ ፕሮግራም (School Breakfast Program) ወይም በብሄራዊ የትምህርት ቤት ምሳ ፕሮግራም (National School Lunch Program) አማካኝነት - ባለፉት 12 ወራቶች ውስጥ — በ'Community Eligibility Provision' በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ጨምሮ - አገልግሎት ለማግኘት ፈቃድ-የተሰጠው።
- ቤተሰቡ፤ ከፌደራል የድህነት መመሪያዎች (Federal Poverty Guidelines) ከ200% ወይም በታች ላይ የሚገኝ ወይም፤ የቤተሰብ አባል - በሌላ የሕዝብ እርዳታ ፕሮግራሞች ውስጥ እንደ - ተጨማሪ ተመጣጣኝ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (Supplement Nutrition Assistance Program)፣ ልዩ የሆነ ተጨማሪ የተመጣጣኝ-ምግብ ፕሮግራም ለሴቶች፣ ህፃናቶች እና ልጆች፣ ሜዲኬድ (Medicaid)፣ ወይም የፌደራል የሕዝብ የመኖሪያ-ቤት እርዳታ (Federal Public Housing Assistance) ባሉት ውስጥ እርዳታ-የሚወስዱ።

ብቁ-የሆነው ቤተሰብ፤ በወር $30 ለኢንተርኔት አገልግሎቶች የሚውል፣ እና የአንድ-ጊዜ የቅናሽ - እስከ $100 - ለላፕቶፕ (laptop)፣ ዴስክቶፕ ኮምፒውተር ወይም ታብሌት (tablet) - የሚያገኙ-ይሆናል። ቤተሰቦች፤ ብቁነታቸውን እና ምዝገባውን፣ በGetInternet.gov ላይ መመልከት ወይም በ877-384-2575 በመደወል ማረጋገጥ-ይችላሉ።

ይህ ጥቅማ-ጥቅም (benefit)፤ ለነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) ብቁነት ለመወሰን ዓላማ እንደ-ገቢ ሆኖ የሚቆጠር አይደለም። ለተጨማሪ መረጃ፤ የተመደበውን-የትምህርት ቤት የአመጋገብ ፕሮግራም (School Nutrition Programs (SNP) - ከልላዊ ባለሞያን፣ ወይም የ'SNP' የፖሊሲ የመላኪያ ሣጥንን በኢሜል በSNPpolicy@doe.virginia.gov እባካችሁ አነጋግሩ።

## የትምህርት ቤት + የሕግ አስከባሪ አጋርነት የዳሰሳ-ጥናትን - እስከ ኦክቶበር (Oct.) 2 ቀን 2022 ድረስ፤ ውሰዱ



ያላችሁን አስተያየት (feedback)፣ በ'School + Law Enforcement Partnership (S+LEP) የዳሰሳ-ጥናት አማካኝነት እባካችሁ - አስገቡ። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ ለቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለማጠናቀቅ ከ10-15 ደቂቃዎችን የሚወስድ እና፣ ከ'S+LEP Advisory Group' ጋር ስለ ትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃ አብሮ ለመስራት-ወሳኝ ነገር ነው።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ዋና-እሴቶቹ አድርጎ ያካተተው፤ ትምህርት ቤታችን ሁሉን የሚቀበል መሆኑን፣ እና ለሁሉም ሰው በደህንነት ተገኝቶ-የሚማርበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ የዳሰሳ-ጥናት የተገኙ ውጤቶች፤ የ'S+LEP Advisory Group'ን፤ በመጪው በዲሴምበር (December) 2022 - በACPS እና በአሌክሳንድርያ የፖሊስ መምሪያ  መካከል እንደገና-እንዲታሰብ በታቀደው አጋርነት፣ ለትምህርት ቤት ቦርዱ ያቀረበውን የአስተያየት-ሃሳቦች ላይ፣ በቀጥታ ለመጠቆም ጥቅም-ላይ ይውላል። በተጨማሪም፤ የዳሰሳ-ጥናት ምላሽ-ሰጪዎች፣ በመጪው የ'focus group' ውይይቶች ላይ - ስለ ትምህርት ቤት እና ክፍሉ (division) ደህንነት እና ጥበቃ ላይ፣ ተካፋይ-የመሆን ፍላጎት እንዳላቸው የሚጠቁም ይሆናል።

ስለ 'S+LEP Advisory Group'፣ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፤ እባካችሁ የACPS ድህረ-ገጽን ጎብኙ።

## የሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ



በሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 ባደረገው-ስብሰባው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ፣ የመጀመሪያው-የሆነውን ተከታታይ - የStrategic Plan Video Vignettesን ይፋ-አድርጓል። ACPS - ስለ ትምህርት ቤት ቦርድ ከክፍል/division ጋር - የACPS 2025: Equity for All Strategic Planን - ዓላማ፣ ራዕይ እና ግቦችን ወደ ሕይወት ለማምጣት እንዴት እንደሚሰራ - የውስጥ-አሰራሩን ምልከታ፣ ለሠራተኞች፣ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላቶች ለማቅረብ - ወርሃዊ የሆኑ ቪዲዮዎችን የሚያጋራ-ይሆናል!

የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ርዕሶች ላይም፣ ምላሽ-ሰጥቶበት ነበር:

- SLEP Advisory Group፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አዲስና-ማሻሻያ
- SY21-22 የደህንነት-ጥበቃ የመረጃ-ስብስብ/ (Q3 እና Q4)

- የፖሊሲ ክለሳዎች (Policy Revisions)

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## የ'Back to School' ቅፃችሁን አጠናቅቁ እና ዓመቱን በጥንካሬ እንድንጀምር እርዱን



ሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ቤተሰቦች፤ አዲሱን የቀለም-ትምህርት ዓመትን በስኬታማነት ለመጀመር - ጠቃሚ የሆነ ሚና ይጫወታሉ። ይህም የመጀመሪያ የቤት ስራቸው የሆነው — የ'Back to School' ቅጾችን ለእያንዳንዱ ተማሪ — እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ፣ መግባት ያለበትን አጠናቅቆ-በማስገባት ነው።

እነዚህ ቅጾች በቀላሉ በኦንላይን ላይ - የ'PowerSchool Parent Access portal'ን በመጠቀም - እንደ በአደጋ-ጊዜ መገኘት የሚችሉ ሰዎች አድራሻዎችን፣ አዲስና-የተሻሻለ (update) የጤና መረጃዎችን እና የመውጣት (opt-out የማድረግ) ምርጫዎችን ያሉትን-ለማረጋገጥ የምትችሉበት ነው። መረጃዎቻችሁ - ከአለፈው-ዓመት የተቀየረ-ነገር ከሌለው፤ እባካችሁ ትክክለኛነትን አረጋግጡል-እና፤ ሁላችሁም በቅርብ-ጊዜ የተስተካከለ መረጃ ለእያንዳንዱ ተማሪ መኖሩን እርግጠኛ ያደርገናል።

እንግሊዘኛ እና ስፓኒሽ-ተናጋሪ ቤተሰቦች - ከኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ (electronic device) ጋር፤ አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾች በ'PowerSchool' ውስጥ ለመሙላት - ከዚህ በታች-ያለውን ማገናኛዎች (links) መጠቀም ይችላሉ:

- እንግሊዘኛ/English 2022-23 የ'Back to School' ቅጾች።
- ስፓኒሽ/Spanish 2022-23 የ'Back to School' ቅጾች።

የአማርኛ - እና አረብኛ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦቻችን፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School' ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በአማርኛ እና አረብኛ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ጥራዙን (a packet) - ከልጃቸው ትምህርት ቤቶች በመጠየቅ ሊያጠናቅቁ-ይችላሉ። እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች - የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ የሌላቸው ከሆኑም፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School' ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በእንግሊዘኛ/English እና ስፓኒሽ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ከትምህርት ቤታቸው የታተመውን ጥራዝ (a packet) በመጠየቅ፣ ማጠናቀቅ-ይችላሉ። ተሞልቶ-የተጠናቀቁ ቅጾች፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ (front office) መግባት-አለባቸው።

# በሴፕቴምበር (Sept.) 15 ቀን 2022 - የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት ደረጃ




እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 15 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 165.0 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብሰቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በሴፕቴምበር (Sept.) 15 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል (Center for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።